**የሲቪል ማኅበራት የጋራ ጥሪ**
**በሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነሮች አሰያየም ሂደት ውስጥ ሴቶች**
**በአመርቂ ሁኔታ እንዲወከሉ ስለመጠየቅ፡**

በቅርቡ የኢትዮጵያ ህዝብ ተወካዮች ም/ቤት  የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ፡ በአዋጅ ቁጥር 1265/2014 ማፅደቁ ይታወቃል። በአዋጁም በኢትዮጵያ በሚገኙ የተለያዩ የፖለቲካ እና የሃሳብ መሪዎች እንዲሁም የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል እጅግ መሠረታዊ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የሚታየውን የሃሳብ ልዩነት እና አለመግባባት ለማርገብ እና ለመፍታት ሰፋፊ አገራዊ የሕዝብ ምክክሮችን አካታች በሆነ መንገድ በማካሄድ አገራዊ መግባባት ለመፍጠር እና ተያያዥ የሆኑ ሃሳቦች የኮሚሽኑ የተቋቋመበት አላማ ተብለው ተቀምጠዋል።

በዓለም ዙሪያ ካሉ ሀገራት የተገኙ ተመኩሮዎች እ ንደሚያሳዩት ሴቶች በብሔራዊ ምክክር፣ እርቅ እና ሰላም ሂደቶች ውስጥ ሲሳተፉ ዘላቂ የሆነ መፍትሄ እና የማይቀለበስ ስኬት የማግኘት ዕድላቸው ሰፊ ነው። የሴቶች ጉዳይ ችላ እንዳይባል ይልቁንም በሂደቶች ሁሉ ውስጥ የሴቶች ጉዳይ እንዲካተት እና ከስርዓተ ጾታ አንጻር የብሄራዊ ውይይት ጉዳዮች እንዲቃኙ የሴቶች ተሳትፎ አስፈላጊ እና የማይተካ ነው። የማኅበረሰቡን ግማሽ ክፍል የሚወክሉ ሴቶች በብሔራዊ ምክክር መድረኮች እና ሂደቶች ላይ ሳይወከሉ ዘላቂ የሆነ ሰላምና መግባባት ማስፈን አይቻልም።ስለሆነም ሴቶች በብሔራዊ ጉዳዮች ውሳኔ ሰጪነት እርከኖች በበቂ ሁኔታ ውክልና ሊሰጣቸው ይገባል። ከዚህም አንፃር የኢትዮጵያ መንግስት በአስተዳደር እና ውሳኔ ሰጨነት እርከኖች የሴቶችን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማረጋገጥ ያሳየውን ቁርጠኝነት እያደነቅን በኮሚሽነሮች አሰያየም ሂደቱም ይህ እንደሚቀጥል ተስፋ እናደርጋለን።

የእጩ ጥቆማው እየተጠናቀቀ ባለበት_ሰዓት_ስማችን ከታች የተመለከተዉ የሲቪል ማኅበራት ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልናቀርብ እንወዳለን፡

1) ዕጩ የኮሚሽን አባላት ከሕዝብ፣ ከፖለቲካ ድርጅቶችና ከሲቪል ማኅበራት ጥቆማ ተሰብስቦ ከእነዚህ ጥቆማዎች አስራ አራት (14) እጩዎችን አፈ ጉባኤው እንደሚያቀርብ ተደንግጓል። ሆኖም እጩዎቹ የሚመረጡበት መስፈርት ግልጽ አልተደረገም። ይህ የመጨረሻ 14 እጩዎች የሚመረጡበት መስፈርት እና ሂደት ግልፅ እና ታዕማኒነት የተሞላበት እንዲሆን እንጠይቃለን።

2) ከዚህ በፊት በረቂቅ አዋጁ ላይ በተደረጉ የውይይት መድረኮች እና የአስተያየት ቅበላዎች የተነሳው በህግ የሚቀመጥ የፆታ ድርሻ (Gender Quota) በፀደቀው አዋጅ ሳይካተት በመቅረቱ በኮሚሽኑ የሚኖረውን የሴቶች አስተዋፅኦ ከለላ አሳጥቷል ብለን እናምናለን። ስለሆነም እጩ ኮሚሽነሮች በሚመረጡበት ሂደት የፆታ ድርሻ የመምረጫ መስፈርት እንዲሆን እንዲሁም የሴት ኮሚሽነር እጩዎች ቁጥር ከወንዶች ጋር የተስተካከለ እና ቢያንስ 50% ሴቶች እንዲሆኑ ስንል ከአደራም ጭምር ልናሳስብ እንወዳለን።

3) በተጨማሪም ኮሚሽኑ የሥርዓተ-ፆታ እና የአካታችነት ጉዳዮችን ጨምሮ በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ግብዓቶችን ማቅረብ የሚችሉ ቴክኒካል አማካሪዎች ድጋፍ እንዲያገኝ እንጠይቃለን።

4) የሴቶች ድርጅቶች እና አደረጃጀቶች እጩዎች በሚጣሩበት ሂደት ውስጥ እንዲወከሉ እና የማጣራቱ ስራ ላይ እንዲሳተፉ እንጠይቃለን።

5) የሴቶች በኢ-መደበኛ እና ባህላዊ የምክክር ሂደቶች ያላቸው ሚና እውቅና እንዲሰጠው ብሎም ሴት የማሕበረሰብ መሪዎች የኮሚሽነሮች እጩዎች ዝርዝር ውስጥ እንዲካተቱ እናሳስባለን።

በመጨረሻም ኮሚሽኑ የተቋቋመበትን አላማ እንዲያሳካ የሲቪል ማኅበራት የበኩላችንን ድጋፍ እንደምናደርግ ልናሳውቅ እንወዳለን።

ጥሪውን ያቀረቡ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዝርዝር፡

1. ፋሚሊ ሰርቪስ አሶሴሽን (FSA)
2. ኤምፓዚ ፎር እንተግሬትድ ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን (ELIDA)
3. ትምራን ኢትዮጵያ
4 ሀድያ ወጣቶች ማኅበር (HYA)
6 የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት(NEWA)
7. ኮንሰርን ፎር ኢንተግሬትድ ዴቨሎፕመንት
8. የኢትዮጵያ ሰባዓዊ መብት ተሟጋቾች ማዕከል (EHRDC)
9. ሴታዊት ንቅናቄ
10. የመብቶችና ዴሞክራሲ እድገት ማዕከል (CARD)
11. ሴቭድ ቱ ሴቭ
12. ሲቪል ሶሳይቲ ሳፖርት ፕሮግራም 2 (CSSP-2)
13. ምዝዝጎዋ የሴቶች ልማት ማኅበር
14. ስራዓተ ፆታና ታዳጊነት፡ አለማቀፋዊ ማስረጃ (GAGE)
15. ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ(AHRE)
16. ሳራ ፍትህ ከሁሉም ማኅበር
17. ጌት ፎር ኦፖርቱኒቲ(GO)
18. ፕሮጀይኒስት(Progynst)
19. ውሜንስ አላያንስ ፎር ፒስ ኤንድ ሶሺያል ጅስቲስ (WAPSJ)
20. ውሜን ካን ዱ ኢት (WCDI)